DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



www.dcps.dc.gov

ጥያቄ አልዎት? በሚከተለው አድራሻ እኛን ለማነጋገር ነጻ ይሁኑ
(202) 719- 6613 ወይም ofpe.info@dc.gov

1200 First Street NE, Washington, DC 20002

/dcpublicschools @dcpublicschools @dcpublicschools

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የወላጅ የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ጽሑፍ



## ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

HS




*ቤት"እያንዳንዱ ወላጅ ስለ ልጃቸው የትምህርት ውጤት በጥልቀት እንደሚያስቡ እናውቃለን። ከቤተሰቦች ጋር በቅርበት የምንሠራውም ለዚሁ ሲባል ነው፤ ምክንያቱም የእነርሱ ተሳትፎ ለልጆቻችን እና ለትምህርት ቤቶቻችን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን።"*

*- ቻንስለር ካያ ሔንዴርሰን*

## የወላጆች የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ጽሑፍን እንዴት መጠቀም ይቻላል፡-

ይህ መመሪያ ጽሑፍ ልጅዎትን በቤት ውስጥ ለመርዳት የሚያስፈልግዎትን ዘዴዎች ያስጨብጥዎታል። በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ፣ ልጅዎት በትምህርቱ ወይም በትምህርቷ መድረስ ካለባቸው ግብ ላይ እንዲደርሱ ለመርዳት በ DCPS ሥርዓተ ትምህርት ላይ መሠረት ያደረጉ መረጃ ስልቶችን ያገኛሉ። ልጅዎት በትምህርት ቤት ምን እየተማረ/ች እንደሆነ እና እርስዎም በቤት ውስጥ በተጨማሪ እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ የተሻለ ግንዛቤ ይኖርዎታል።

በተጨማሪም፣ ይህ መመሪያ ጽሑፍ ዋና ዋና ለሆኑ የቤት ሥራዎቻችን በቤት ውስጥ መሥራት እንዲቻል የሚረዱ በግልጽ የተቀመጡ ስልቶችን ይሰጣል። ዋና ዋና የቤት ሥራዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው፣ በእያንዳንዱ የጥናት ክፍለ ጊዜ ሁሉ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሚሳተፉበት በግዛቱ በሙሉ ጥልቀት ያለው እንቅስቃሴዎች የሚቀርቡባቸው ናቸው። ልጅዎት ሊያጋጥሙት የሚችሉ አራት ዋና ዋና (Cornerstones) የቤት ሥራዎች ናሙናዎችን ከጠቃሚ ምክሮች እና በቤት ውስጥ እንዴት ሊረዱት እንደሚችሉ ከሚጠቁሙ ሐሳቦች ጋር አያይዘን አቅርበንልዎታል።

ስለዋና ዋና ሥራዎች (Cornerstones) ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት bit.ly/DCPSCornerstonesVid የሚለውን ይጎብኙ።

## ምን ማድረግ ይችላሉ፡

በልጅዎ የትምህርት ችሎታ ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሚና እርስዎ ይጫወታሉ። በቤት ውስጥ ትምህርትን ለማገዝ ሊያደርጉዋቸው የሚችሉዋቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው፡-

- ትምህርት የስኬት መሠረት መሆኑን ልጅዎ እንዲረዳ ማድረግ።
- ልጅዎ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ምን እንዲማር እንደሚጠበቅበት ይወቁ።
- ልጅዎ ከፍተኛ የሆነ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ የትምህርት ግቦችን እንዲያስቀምጥ ይርዱት።
- የቤት ሥራውን ለመጨረስ የሚያስችለው በቂ የሆነ ጊዜ እና ቦታ ይስጡት።
- በትምህርት ቤት ውስጥ ምን እየተከሰተ እንዳለ ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ እንዲሁም በቋሚነት መሻሻሎችን ይከታተሉ።
- ስለ ልጅዎ ይከራከሩ።
- የልጅዎን ጠንካራ ጎኖች ለልጅዎ መምህር ያካፍሉዋቸው።

## ለልጅዎ መምህር የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች፡-

ስለ ትምህርት እድገት ወይም ስለ ለውጥ ከልጅዎ መምህር ጋር በሚነጋገሩበት ወቅት እንደ ጥያቄ ሊያቀርቧቸው ግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚችሉ ጥቂት ጥያቄዎች እዚህ ላይ ተሰጥተዋል፡-

- የትምህርት ግቦች ምንድን ናቸው? የትምህርት ዓላማዎችን የሚያሳኩ የተማሪ ሥራ ምሳሌዎችን ሊያሳዩኝ ይችላሉን?
- የልጄን ሥራ ምሳሌ ማየት እችላለሁ? እነዚህን የትምህርት ዓላማዎች የሚያሳካው ወይም የማያሳካው በምን ሁኔታ ነው?
- ልጄ በክፍል ደረጃው ልክ ወይም ከደረጃው በላይ ነው ያለው? ምን ተጨማሪ ድጋፍን ማግኘት ይቻላል? ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁ?
- ቤት ውስጥም ተግባራዊ መሆን ያለባቸው የክፍል ውስጥ መደበኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- ልጄን በየቀኑ እርስዎ ስለሚሰጡት ትምህርት ምን ዓይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ እችላለሁ?

## ከእርስዎ ልጅ ጋር መነጋገር፡-

መልካም ውይይቶች ልጆቻችን ስለ ሕይወታቸው እንደምናስብ ወይም እንደምንጨነቅ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ውይይት ለማስጀመር ያህል መጠየቅ የሚችሏቸው ጥቂት ርዕሰ ጉዳዮች እነዚህ ናቸው፡-

- በትምህርት ቤት ይበልጥ ስኬታማ እንድትሆን እንዳግዝህ ምን ላደረግ እችላለሁ?
- በትምህርት ቤት ከምትማራቸው ጽንሰ ሐሳቦች መካከል ያስቸገረህ ነገር አለ?
- በሚቀጥለው ወር ሠርተህ ማስረከብ ያለብህ የሆነ ፕሮጀክት አለ? ፕሮጀክቱ(ቶቹ) ላይ ሥራ መሥራት ጀምረሃል?
- በቅርቡ የምትፈተነው ፈተና ወይም ሙከራ አለህ? በምን ትምህርቶች ላይ? ፈተናውን በደንብ እሠራዋለሁ ብለህ ታስባለህ?

## አልጀብራ I ኮርነርስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን፣ የአንዲት ከተወሰነ ከፍታ ላይ በቀጥታ ዝምብላ የወደቀች አሻንጉሊትን በተመለከተ ውሂብ (ዴታ) ተማሪዎች ይሰበስባሉ። ተማሪዎች የብር ላስቲክ “ተወዛዋዥ ክር” ለመፍጠር የሚጠቀሙ ሲሆን ይኸውም አሻንጉሊቷ መሬት ሳትነካ ነገር ግን በሚቻል ቅርበት ድረስ ወደ መሬት ቁልቁል እንድትጓዝ ለማድረግ ያስችላቸዋል። ለዚህ ተግባራዊ ልምምድ ስኬታማ ዕቅድ ለመፍጠር እንዲችሉ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ተማሪዎች በርካታ ሙከራዎችን ያካሂዳሉ እንዲሁም ትንታኔ ይሰጣሉ።

### ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- ስለ አልጄብራ ጠቃሚ ምክሮችን እና ስትራቴጂዎችን እንዲያገኝ ልጅዎን khanacademy.com እንዲጎበኝ ያድርጉት።
- አካዳሚያዊ ስኬት ለማግኘት የሚያስችል ዕቅድ ለማውጣት ከልጅዎ መምህር ጋር ይነጋገሩ። ከልጅዎ መምህር ጋር በመሆን በግል የሚሰጥ ትምህርትን ወይም በመደበኛነት የሚከናውን ፍተሻን የሚያካትት አካዳሚያዊ ዕቅድ ያውጡ።
- የእርስዎ ልጅ ስለ Barbie Bungee Project በመስመር ላይ (ኦንላይን) የሚሰጠውን ሰርቶ ማሳያ ተግባራዊ ትምህርት በሚከተለው አድራሻ ላይ እንዲመለከት ያድርጉት፦ www.youtube.com/watch?v=YmjhGYoP-2E

## ባይሎጂ ኮርነርስቶን

በዚህ ኮርነር ስቶን፣ የራሳቸውን የጋዝ ልቀት (carbon footprints) ዱካ ለመከታተል፣ ውጤቱን በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ሌሎች ተማሪዎች ጋር ለማወዳደር፣ እና ከዓለም አቀፍ ተማሪዎች ጋር በመስመር ላይ (ኦንላይን) በሚከፈቱ የውይይት መድረኮች ላይ መስተጋብራዊ የመልእክት ልውውጥ እንዲያደርጉ International Student Carbon Footprint Challenge የተባለውን የድርጣቢያ ተማሪዎች ይጠቀማሉ።

### ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- የቤተሰባችሁን የጋዝ ልቀት (carbon footprint) መጠን ለማስላት በመስመር ላይ (ኦንላይን) የ Family Carbon Footprint መልመጃን ይሙሉ። በዚህ መልመጃ ላይ፣ እርስዎ እና የእርስዎ ልጅ በአካባቢ ላይ የምታሳድሩትን አሉታዊ ተጽዕኖ መቀነስ የምትችሉባቸውን መንገዶች ትማራላችሁ። በዚህ ልምምድ ላይ የሚሰበሰበው ውሂብ (ዴታ) ለልጅዎ ኮርነር ስቶን ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

## አልጀብራ II ኮርነርስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን ላይ የእነርሱን የሕይወት ዘመን የገንዘብ ገቢዎችን በተለያዩ የሙያ ፈለጎች ሞዴል ለማድረግ፣ ሊሰማሩ በሚፈልጉት ሙያ አንጻር የሚያስፈልገውን የከፍተኛ ትምህርት ወጪ ለማስላት ሊኒያር ፋንክሽስን (linear functions) ተማሪዎች ይጠቀማሉ። በፕሮጀክቱ መጨረሻ ላይ፣ እያንዳንዱ ተማሪ የሚፈለገውን የሙያ ፈለግ ዝርዝሮች የሚያብራራ፣ የመረጠውን ኮሌጅ እና የኮሌጅ እና የሙያ ምርጫን ወጪ ሁለቱንም በሒሳብ ሙያ በሚደግፍ መልኩ የሚቀርብ ትንታኔን ያካተተ በጽሑፍ፣ በፖስተር ወይም በPowerpoint ቅርጽ የተዘጋጀ ሪፖርት ያቀርባል።

### ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- የ U.S Bureau of Labor Statistics’ occupational outlook handbook www.bls.gov/ooh/ ይጎብኙ እና የሙያ ፈለጎችን በተመለከተ ከልጅዎ ጋር ይወያዩ። ልጅዎ ሲያድግ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ይጠይቁት። ከፍተኛ ተከፋይ፣ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ያለ እና በጣም በቅርቡ ይፈጠራሉ ተብለው ስለሚገመቱ አዳዲስ ሥራዎች በመከፋፈል የሙያ ፈለጎች ላይ ምርምር ያድርጉ።

## የኬምስትሪ ኮርነር ስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን ላይ ተማሪዎች ተግባራዊ ኤሌክትሪካዊ ሕዋሳትን ይፈጥራሉ እና የእያንዳንዱን ሕዋስ ተነጻጻሪ ጥንካሬ ምን እንደሆነ ለይተው ያውቃሉ።

### ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- በቀላል የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች በመጠቀም ባትሪ ለመሥራት ከልጅዎ ጋር በይነመረብ (ኢንተርኔት) ላይ ዘዴዎችን ይፈልጉ። የራስዎን ዘመናዊ ስልክ (ስማርትፎን) ኃይል ለማጎልበት ምን ዓይነት ቁሳቁሶች እንደሚያስፈልጋችሁ ለይታችሁ እወቁ።

## የአንድ ዓመት ጊዜ ርዝመት ያለው የትምህርት ጠቃሚ ምክር

- ልጅዎ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት እንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጥ ያግዙት። ከትምህርት ቤት ጋር ተዛማጅነት የሌላቸውን ተግባራት ጨምሮ ልጅዎ በሳምንቱ ውስጥ ማከናወን ያለበትን ወይም ያለባትን ሁሉንም ነገሮች እንዲጽፍ/ድትጽፍ ይጠይቁት/ቋት። የእርስዎ ልጅ እያንዳንዱን ተግባር ከ 1 እስከ 4 መለያ እንዲሰጠው/ድትሰጠው ያድርጉ፤ 1 እንደ በጣም አስፈላጊ ይቆጠራል። ልጅዎን ያግዙት የበለጠ አካዳሚያዊ ስኬት እንዲያገኝ ቅድሚያ ተሰጪ ነገሮችን ቅድሚያ እንዲሰጥ እና ዝርዝሩን እንደገና 1 ቁጥር የተሰጣቸውን ከላይ በማድረግ ደግሞ እንዲጽፍ ይንገሩት። ደጋግመው በጊዜ ሂደት ዝርዝር እንዴት በተግባር ላይ እያዋለ እንዳለ ያረጋግጡ።

## ጂኦሜትሪ ኮርነ ርስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን ተማሪዎች ካርታን ለመዳሰስ ፕሮትራክተሮችን እና መግነጢሳዊ ኮምፓስን ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በካርታ ላይ የተጠቆሙ ተከታታይነት ያላቸው ነቁጦችን ፈልገው ያገኙ እና በጣም አጭር ጊዜ የሚወስዱ የጉዞ መስመሮችን ዕቅድ ያወጣሉ።

### ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- በ LearnZillion.com ላይ የራስዎን መለያ (አካውንት) ይፍጠሩ። ጣቢያው የእርስዎ ልጅ በቤት ውስጥ የሚማረውን ትምህርት ሊያጠናክሩት የሚችሉ በጣም ጥሩ የቪዲዮ ሥርቶ ማሳያ ትምህርቶች አሉት።



## የ ፊዙክስ ኮርነ ርስቶ ን

በዚህ ኮርነርስቶን፣ ተማሪዎች ለመኪና አሽከርካሪዎች ትምህርት መምህራን ቡድን ያላቸውን የፊዚክስ ዕውቀት በተግባር ያሳያሉ። መምህራኑ ርቀትን መስበር፣ ሰበቃ እና ኩርባዎችን፣ ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ ከኋላ የመከተል ርቀት፣ እና የቢጫ መብራት መንገድ ማቋረጫዎችን የተመለከቱ ፊዚክስ ነክ የተማሪውን ዕውቀት በቃል እና በጽሑፍ በሚሰጡ ቀራቢ ዝግጅቶች በመጠቀም ይገምግማሉ።

### ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- ልጅዎ የፍጥነት እና የሰበቃን ፊዚክስ በእውነተኛ ተሽከርካሪ ላይ ደህንነቱ እንደተጠበቀ ተግባራዊ ማድረግ ወደ የሚችልበት ወደ go-kart race ይውሰዱት። እንዲህ የመሰለውን አስደሳች ጊዜ ማሳለፊያ ማግኘት የሚችሉበት በርካታ ከቤት ውጭ የሚከናወኑ (እንዲሁም ጥቂት ደግሞ በቤት ውስጥ የሚከናወኑ) የእሽቅድምድም መሞች (ትራኮች) በዲሲ አካባቢ ይገኛሉ።
- ልጅዎ Stop or Speed Through a Yellow Light ን በሚከተለው አድራሻ ላይ እንዲያነብ ያበረታቱት፦ www.sciencedaily.com/releases/2010/06/100608162244.htm።

### የአንድ ዓመት ጊዜ ርዝመት ያለው የትምህርት ጠቃሚ ምክር፦

- የጊዜ በአግባብ አጠቃቀም ላይ ያግዙ። አብዛኞዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የቤት ሥራ እና ከሥርዓተ ትምህርት ውጪ የሆኑ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ቀላል የማይባል ጊዜ ይጠፋሉ። ልጅዎ የጥናት ዕቅድ እንዲፈጠር በማድረግ የጊዜ በአግባብ አጠቃቀም ክህሎቶችን እንዲያጎለብት ያግዙት።
- ልጅዎ ከፍተኛ አካዳሚያዊ ግቦችን እንዲያስቀምጥ ያግዙት። በእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ የሚመዘንበት ክፍለ ጊዜ፣ ልጅዎ በእያንዳንዱ ኮርስ ላይ ምን ውጤት ማግኘት እንዳለበት ወይም እንዳለባት እንዲወስን ወይም እንድትወስን ያግዙት/ያግዟት። ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉ ግቦችን ማለም ልጅዎ እርስዎ ምን እንደሚጠብቁ እንዲገንዘብ ይረዳዋል። ግቦች በተጨማሪ የመሥራት ፍላጎቱን የሚያነሳሳ የሆነ አዎንታዊ ነገር ይስጡት። ልጅዎ ያስቀመጠውን ግቦች ለመምታት ጠንክሮ መሥራት መቀጠሉን ለማረጋገጥ በየሩብ መንፈቅ ዓመቱ ላይ እነዚህን ግቦች በተመለከተ አስተያየት መስጠትን ከግምት ያስገቡ። "በዚህ ትምህርት በረዥም ጊዜ ልታሳካው የምትፈልገው ግብ ምንድን ነው? የረዥም ጊዜ ግብህን እንደምትመታ እርግጠኛ ለመሆን ምን የአጭር ጊዜ ግቦች ማስቀመጥ ይኖርብናል? በትክክለኛው ጎዳና ላይ እንዳለህ እርግጠኛ ለመሆን ግስጋሴህን እንዴት ልንፈትሸው እንችላለን?
- ሁሉንም የተርም አጋማሽ ሪፖርቶች እና ሪፖርት ካርዶችን ይመልከቱ።
- በትምህርት ቤት ምን እየተፈጠረ እንዳለ እና ጥሩ አዳማጭ እንዲሆን ልጅዎን ያነጋግሩት። ልጅዎ በሚጠቀማቸው ቃላት ላይ ብቻ ሳይሆን ልጅዎ የሚጠቀማቸውን አካላዊ ቋንቋ፣ አዝማሚያ እና ስሜት ላይም ትኩረት ይስጡ።

# እን ግሊዜኛ I ኮርነ ርስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን፣ ተማሪዎች Fences በተባለው ተውኔት ላይ ካሉት ገጸ ባህሪያት አንዱን በቅርበት ይመለከታሉ እና ኦገስት ዊልሰን ያንን ገጸ ባህሪ እንዴት ከግል ወይም ከማኅበራዊ ውጥረት ጋር የተቆራኘ ጭብጥን ለማጎልበት እንደተጠቀመበት ይመረምራሉ። ተማሪዎች እንዴት አንድን ተለይቶ የታወቀ ጭብጥ ለማጎልበት የገጸ ባህሪ መስተጋብሮች፣ ቃላት እና/ወይም ድርጊቶች እንደሚያገለግሉ ትንታኔ ይሰጣሉ። ተማሪዎች ትንታኔያቸውን በገጸባህሪ-ጭብጥ ጽንሰ ሐሳብ በተነደፈ ካርታ በመጠቀም ያቀርባሉ።

## ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- ከልጅዎ ጋር ስለ Fences ይወያዩ – ስለ ተውኔቱ ምን ያስባል? የእርስዎ ልጅ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስለሚፈጥረው የውጥረት ገበታ የሚያስበውን እንዲያካፍልዎት ይጠይቁ።
- ልጅዎ ለቤተሰብ አባላት ያዘጋጀውን የገጸ ባህሪ ጭብጥ ቀራቢ ዝግጅት እንዲያቀርብ ያበረታቱት።
- ከኦገስት ዊልሰን Fences የተወሰዱ ቅንጥብ ፊልሞችን bit.ly/DCPSFences ላይ መመልከትን እና በዚያ ትዕይንት ላይ ያለውን ውጥረት መወያየትን ከግምት ያስገቡ።

# እ ን ግሊዜኛ II ኮር ነ ርስ ቶን

በዚህ ኮርነርስቶን The Things They Carried የሚባለውን መጽሐፍ ያነባሉ እና ከቬትናም ጦርነት ወይም ተመሳሳይ አመጾች ጋር ግንኙነት ባለው ክስተት የተነሳ ፎቶን በጥንቃቄ ይመለከታሉ። ተማሪዎች ስለፎቶግራፉ ትርጉም እና ስለፎቶግራፍ አንሺው የጦርነት አመለካከት ወደ ውይይት ሊያመሩ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ይፈጥራሉ።

## ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፦

- ልጅዎ በዚህ ኮርነርስቶን ላይ ደራሲ ቲም ኦብራይን ስለ The Things They Carried www.youtube.com/watch?v=B8ivNokqT74 የተባለው ፊልሙ ማብራሪያ ሲሰጥ እንዲመለከት በማድረግ ጠቃሚ የዳራ መረጃ እንዲኖረው ያድርጉት።



## የአንድ ዓመት ጊዜ ርዝመት ያለው የትምህርት ጠቃሚ ምክር፦

- ራስን ችሎ ፕሮብሌም አፈታትን እንዲያጎለብት ያበረታቱት። የራሳቸውን ችግሮች ራሳቸው መፍታት መቻላቸው ተማሪዎች በራስ መተማመንን እንዲጎናጸፉ እና ይበልጥ ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።
- የወላጅ መምህራን ውይይቶች በሚገባ ይጠቀሙባቸው። የወላጅ መምህር ውይይቶች ተማሪ ስኬታማ እንዲሆን ለወላጆች እና ለመምህራን አብረው እንዲሠሩ ለየት ያለ አጋጣሚን ይፈጥርላቸዋል። ለተማሪ ስኬት እንዲረዳ ዕቅድን በጋራ ለማጎልበት የተወሰነ ጊዜ ለማጥፋት ከግምት ያስገቡ። የጥያቄዎች እና የሚያስስቡ ነገሮች ዝርዝር ማለትም እንደ "የእኔ ልጅ በምን አካባቢዎች ላይ መሻሻል ያስፈልገዋል?" ወይም "በቤት ውስጥ ልጄን እንዴት ማገዝ እንደምችል የሚጠቅመኝ ሊሰጡኝ የሚችሉት ምክር አልዎት?" የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ማዘጋጀትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
- ከልጅዎ መምህር ጋር በቀጣይነት መልእክት እየተለዋወጡ ግንኙነትዎን አጥብቀው ይቀጥሉ። የሚከተለውን ጥያቄ መጠይቅን ከግምት ያስገቡ፦ "በእርስዎ መማሪያ ክፍል ውስጥ ልጄ ስኬታማ እንዲሆን ለማገዝ ሐሳቦችን አንድ ላይ ዝምብለን ብናፈልቅ ያግዛል ብለው ያምናሉ?"
- ትምህርት ቤትዎ EngradePro የሚባል አዲስ ዲጂታል የክፍል መጽሐፍ እንዳለው ያውቃሉ? EngradePro በንቡር ጊዜ ወላጆች የተማሪ ግስጋሴን እንዲቆጣጠሩ ያስችላቸዋል። እርስዎ የልጅዎን ውጤቶች፣ የተሰጡ ሥራዎች ማየት እና ወደ መምህሩ በቀጥታ መልእክቶችን መላክ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እና የእርስዎን የተጠቃሚ ስም እና የይለፍ ቃል ለማግኘት፣ እባክዎ የእርስዎን ልጅ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።
- የእርስዎ ልጅን ያብቁት። "እኔ ማየት ያለብኝ በጣም ወሳኝ መምህር የትኛው ናቸው?" ወይም "ስኬታማ እንድትሆን እንዳግዝህ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?" በማለት ይጠይቁት።

# የ ጤና ኮርነ ርስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን ተማሪዎች በአደጋ ጊዜ በቤት ወይም በሥራ ቦታ ላይ ምን ዓይነት ዝግጅት ማድረግ እና ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ይማራሉ። በዚህ ምዕራፍ ላይ፣ ተማሪዎች እጆች ብቻ CPR እና የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና እርዳታን የሚያካትት የአደጋ ጊዜ ችግሮችን መፍቻ ስትራቴጂዎችን ይማራሉ። በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ቤታቸው ስለሚኖረው ሁኔታ፣ እና ስለ ሕጻን ደህንነት ያለውን ሁኔታ ይመረምራሉ እና በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሕጻናት ደህንነት መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያስችል ዕቅድ ለቤተሰባቸው ያዘጋጃሉ።

## ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፡-

- CPR ይማሩ እና የእርስዎን ቴክኒክ ሂስ እንዲሰጥበት ያድርጉ።
- ቤተሰቦች ወደፊት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን እጆች-ብቻ CPR ክህሎቶች በተጨማሪ ሊማሩ ይችላሉ። ቪዲዮዎች እና የተግባር ማሳያዎች www.heart.org ላይ ሊገኙ ይችላሉ።

# የ ሙዚቃ ኮርነ ርስቶን

በዚህ ኮርነርስቶን፣ ተማሪዎች ለሙዚቃ ፌስቲቫል ልምምድ በማድረግ፣ የሚያቀርቡትን ዝግጅት በመቅረጽ፣ የሚያቀርቡትን ዝግጅት ባስቀመጡዋቸው መስፈርቶች መሠረት በመገምገም እና ገንቢ የሆነ ሂስ በመጠቀም ለሙዚቃ ፌስቲቫል ራሳቸውን ያዘጋጃሉ። ለቀጣይነት ያለው መሻሻል የግብረመልስ ዑደት ከፌስቲቫሉ የሚቀርበበት ጊዜ በፊት ተፈጻሚ ይሆናሉ እና ከፌስቲቫሉ በኋላ በዳኖች የተሰጡ አስተያየቶች የተማሪን የአፈጻጸም ብቃት ለማሻሻል ጥቅም ላይ ይውላሉ።

## ልጅዎን እንዴት ማገዝ ይችላሉ፡-

- ይህ ኮርነርስቶን በ DCPS የሙዚቃ ፌስቲቫል ለመሳተፍ በሚደረግ ዝግጅት ላይ ሂስ አዘል ግብረመልስን ተማሪዎች ለመስጠት፣ ለመስማት እና ተፈጻሚ ለማድረግ ያላቸውን ችሎታ ማጎልበትን ያካትታል። ሂስ አዘል ግብረመልስ ልማዶች ከቤተሰብ ጋር መጋራት ይቻላል። ቤተሰቦች የተማሪዎችን ልምምድ መስማት እና ግብረመልስ መስጠት ይችላሉ።
- በሙዚቃ ውስጥ በጥልቀት ይበልጥ ተሳትፎ ያላቸው ቤተሰቦች ለፕሮጄክቱ በሚጠቅም መልኩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያላቸውን ሥራ ለተማሪዎች እንዲያካፍሉ ሊጋበዙ ይችሉ ይሆናል።

## የአንድ ዓመት ጊዜ ርዝመት ያለው የትምህርት ጠቃሚ ምክር፡-

- ልጅዎ ለማጥናት ጸጥታ ያለው እና በደንብ ብርሃን ያለው ቦታ እንዳለው ያረጋግጡ። ልጅዎ ቴሌቪዥን እንደበራ ወይም ሌሎች ሐሳብን የሚሰርቁ ነገሮች ባሉባቸው ቦታዎች እንዳያጠና ያድርጉ።
- ልጅዎ በመደበኛነት በጥናት መካከል እረፍት እንዲወስድ ይፍቀዱለት። ተማሪዎች ከእያንዳንዱ የ45 ደቂቃ ጥናት በኋላ ለ10 ደቂቃዎች እረፍት ማድረግ አለበት።
- ልጅዎ ፕሮብሌሞችን ራሱ መፍትሔ ወይም መልስ እንዲያገኝላቸው እንዲታገል ይተውት። ልጅዎት ለእርዳታ ሲጠይቅዎት፣ አቅጣጫ አሳዩት፣ ቀጥታ መልሶችን ግን አይስጡት። ልጅዎን በሚያግዙበት ጊዜ እንደ “የት ነው የምትጀምረው?” ወይም “መልሱን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ልታሳየኝ ትችላለህ?” የመሳሰሉ መሪ ጥያቄዎችን በማቅረብ የማሰብ ሂደቱን አቅጣጫ ያስይዙለት።



# የቤተሰብ ኮሌጅ ዕቅድ፡-
## 9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች

ይህ ክፍል የተዘጋጀው በ DCPS እና በኮሌጅ ቦርድ መካከል ባለው የትብብር ስምምነት ነው።

በ2020፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከሚኖሩት ሥራ መስኮች 76 በመቶ የሚሆኑት ከሁለተኛ ደረጃ በተወሰነ መልኩ ከፍ ያለ ትምህርት መማርን የሚጠይቁ ይሆናሉ። ሁሉም ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በእነዚህ የሥራ ዘርፎች ብቁ እንዲሆኑ እና ለስኬታማነት እንዲዘጋጁ እንፈልጋለን። ይህ ግብዓት ወላጆች እና ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለማገዝ እንዲችሉ የእርስዎንልጅ ወደ ኮሌጅ እና በኮሌጅ ውስጥ በስኬታማነት እንዲጓዝ ደጋፊ መረጃን ይሰጣል።



## በጋ

☐ **የኮሌጅ ግቢ ከልጅዎ ጋር ይጎብኙ።**
የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በዓለም ካሉ ምርጥ ኮሌጆች መካከል የሚጠቀሱ አንዳንድ ኮሌጆች አሉት፣ እና የኮሌጅ ግቢዎችን በዲሲ ውስጥ እና በአካባቢዋ መጎብኘት ልጅዎ ወደ ኮሌጅ ገብቶ ለመማር ጉጉት እንዲያድርበት ለማድርግ ጥሩ ዘዴ ነው። በኮሌጅ ውስጥ የሚደረጉ ጉብኝቶች ነጻ ናቸው እና ሁሉም በማናቸውም ዕድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች እንደ የኮሌጆቹ "ዕጩ ተማሪዎች" ተደርገው ይቆጠራሉ። ከመጨረሻው የትምህርት ክፍል በፊት ሁሉንም ኮሌጅ ለመጎብኘት ዒላማ ያድርጉ።

- American University (Red Line—Tenley-town/AU Metro)
- Catholic University (Red Line—Brookland/CUA)
- Howard University (Yellow/Green—Shaw-Howard U)
- George Washington University (Orange/Blue/Silver—Foggy Bottom)
- Georgetown University (D6 or Circulator)
- Marymount (Orange/Silver Line—Ballston Station)
- Trinity Washington University (Red Line—Brookland/CUA)
- University of Maryland (Green Line—College Park/U of MD)
- University of District of Columbia (Red Line—Van Ness/UDC)

☐ **ልጅዎ እንዴት የሥራ መስክ ሐሳቦችን መዳሰስ እንደሚችል ያሳዩት።**
እሱ ወይም እሷ የፍላጎቶች፣ የተሰጥዖዎች እና ተወዳጅ እንቅስቃሴዎች ዝርዝርን ማዘጋጀት እና እነዚህ ከሙያ ዓይነቶች ጋር ማዛመድ መጀመር ይችላሉ። የእርስዎ ልጅ እንዴት ሁሉንም የDCPS የሥራ መስክ ግብዓቶች በ Family Connections ትር ላይ በ Naviance bit.ly/DCPSFamilyConnection. ውስጥ እንዴት መድረስ እንደሚችል ተጨማሪ ይወቁ።

☐ **ለኮሌጅ ትምህርት ምን ወጪዎች እንደሚያስፈልጉ ተጨባጭ እውነቶችን ያግኙ።**
የ U.S Department of Education's College Affordability እና Transparency Center ን በ bit.ly/DCPSAffordability ላይ ይጎብኙ። እርስዎ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ምን ያክል በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገኝ እንደሚችል ሲያውቁ ሊገረሙ ይችሉ ይሆናል። Understanding College Costs የሚለውን በ bit.ly/DCPSUnderstandCost ላይ በማንበብ ይጀምሩ።

# የቤተሰብ የኮሌጅ ዕቅድ

CollegeBoard

ይህ ክፍል የተዘጋጀው በ DCPS እና በኮሌጅ ቦርድ መካከል ባለው የትብብር ስምምነት ነው።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## በልግ (ፎል)

- [ ] **የእርስዎ ልጅ ከትምህርት ቤቱ አማካሪ (ካውንስለር) ጋር እንደተገናኘ እርግጠኛ ይሁኑ**
የእርስዎ ልጅ ስለ ኮሌጅ እና የሥራ መስክ አማራጮች ለመነጋገር እና ይበልጥ ተገቢነት ያላቸው ትምህርቶችን እንዲመርጥ ከአማካሪው ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ መያዝ አለበት። ስለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ ሚና በ bit.ly/DCPSCounselor ተጨማሪ ይረዱ።

- [ ] **ልጅዎ በኦክቶበር ወር ለሚሰው የ PSAT ፈተና ዝግጁ እንዲሆን ያግዙት።**
ሁሉም የ DCPS ከ9ኛ – 11ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በነጻ የ PSAT ፈተናን በኦክቶበር ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት ክፍት የሚሆንበት ቀን ይወስዳሉ። ይህ ተማሪዎች ለSAT እንዲለማመዱ እና ያላቸውን አካዳሚያዊ ዕውቀት እንዲገመግሙ የሚያግዝ በቅድሚያ የሚሰጥ የመለማመጃ ፈተና ነው። በፈተናው ጥሩ ውጤት የሚያገኙ ተማሪዎች በተጨማሪ ለነጻ የትምህርት ዕድሎች ብቁ ይሆናሉ። ስለ PSAT ተጨማሪ መረጃ bit.ly/DCPSPSAT ላይ ያግኙ። ልጅዎን ለ SAT እንዲዘጋጅ ለማገዝ የ Khan Academy/College Board Test Prep Program khanacademy.org/test-prep/sat ን ይመልከቱ፣ ይህ ለሁሉም የኮሌጅ ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ የሚሰጥ ነው።

## ክረምት

- [ ] **ስለ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ማሰብ ይጀምሩ።**
የኮሌጅ ወጪዎችን ለመሸፈን ሊያግዝዎት የሚችሉ የእርዳታ ዓይነቶችን ለማፈላለግ ጊዜው ገና አይደለም። አስቀድመው 7 Things You Need to Know About Financial Aid bit.ly/DCPSFinancialAidInfo. የሚለውን በማንበብ ይጀምሩ።

- [ ] **የዲሲ የነዋሪዎች የትምህርት ዕድሎችን እና ነጻ ትምህርት ዕድል ልገሳ ፕሮግራሞችን ይመርምሩ።**
የዲሲ ነዋሪዎች በ OSSE፣ DC TAG bit.ly/DCPSDCTAG እና Mayoral Scholars በኩል ሁለት ልዩ የነጻ ትምህርት ዕድል ልገሳ ፕሮግራሞች አላቸው እንዲሁም በርካታ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ The United Negro College Fund www.uncf.org እና በ The Hispanic Scholarship Fund www.hsf.net በኩል ለሚተዳደሩ የነጻ ትምህርት ዕድሎች ከውድድር ውስጥ ይገባሉ።

## ጸደይ (ስፕሪንግ)

- [ ] **የእርስዎ ልጅ የኮሌጅ ዝርዝር ማዘጋጀት እንዲጀምር ያግዙት።**
ከልጅዎ ጋር በመሆን እንዴት የኮሌጅ ፍለጋ ማድረግ እንደሚቻል እና ለልጅዎ በጣም አንገብጋቢ የሚሆነውን ነገር በተመለከተ ጠቃሚ ምክሮችን ለማግኘት ኮሌጅ በመምረጥ ላይ bit.ly/DCPSCollegeSearch የኮሌጅ ፍለጋ ደረጃ በደረጃን ይጎብኙ።

- [ ] **ለኮሌጅ ምን ያክል ገንዘብ መቆጠብ እንዳለብዎት ይወቁ።**
የኮሌጅ ገንዘብ ቁጠባ ሒሳብ ማሰቢያ ማሽኑን ከእርስዎ የቁጠባ ግብ አኳያ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ bit.ly/DCPSCollegeCalculator ላይ ይጠቀሙበት።

- [ ] **ልጅዎ የበጋ ዕቅዶችን እንዲያወጣ ያግዙት።**
በጋ ፍላጎቶች ምን እንደሆኑ መርምሮ ለማወቅ እና አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር ትክክለኛው ጊዜ ነው እና ኮሌጆችም ትርጉም ያለው የበጋ እንቅስቃሴዎችን ያደረጉ ተማሪዎችን ይፈልጋሉ። የእርስዎ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ልጅዎ በዚህ በመጪው በጋ ፍላጎቱ የተነሳሳ እንዲሆን ማድረግ የሚችሉባቸውን አምስት መንገዶች bit.ly/DCPSSummer ላይ ያግኙ፣ የ DC Summer Youth Employment bit.ly/DCPSsyep ጭምር ከግምት ያስገቡ። NAF Academy ተማሪዎች ከእነርሱ የኮሌጅ እና የሥራ መስክ አስተባባሪ ጋር ስለ በጋ NAF የትምህርት ላይ እያሉ የሥራ ልምምድ (internships) በተመለከተ መነጋገር አለባቸው። ያስሱ ነጻ ድርብ የበጋ ምዝገባ UDC-CC bit.ly/DCPSDualEnrollment ላይ እና በአካባቢ ባሉ ኮሌጆች ስላሉ ዕድሎች Family Connection ን በድረገጽ አድራሻ bit.ly/DCPSFamilyConnection ላይ ወይም College Greenlight for Nation Wide Opportunities bit.ly/DCPSSummerProgFinAid ላይ ፍለጋ ያድርጉ።

ነጻ የኮሌጅ ዕቅድ አወጣጥ ግብዓቶችን ለማግኘት ይህን ይጎብኙ:-

**bit.ly/DCPSCollegePrep9**

**bit.ly/DCPSCollegePrep10**

# የቤተሰብ ኮሌጅ ዕቅድ፡-
## 11ኛ ክፍል

ይህ ክፍል የተዘጋጀው በ DCPS እና በኮሌጅ ቦርድ መካከል ባለው የትብብር ስምምነት ነው።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

በ2020፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከሚኖሩት ሥራ መስኮች 76 በመቶ የሚሆኑት ከሁለተኛ ደረጃ በተወሰነ መልኩ ከፍ ያለ ትምህርት መማርን የሚጠይቁ ይሆናሉ። ሁሉም ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በእነዚህ የሥራ ዘርፎች ብቁ እንዲሆኑ እና ለስኬታማነት እንዲዘጋጁ እንፈልጋለን። ይህ ግብዓት ወላጆች እና ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለማገዝ እንዲችሉ የእርስዎን ልጅ ወደ ኮሌጅ እና በኮሌጅ ውስጥ በስኬታማነት እንዲጓዝ ደጋፊ መረጃን ይሰጣል።



## በጋ

☐ **የዲሲ የነዋሪዎች የትምህርት ዕድሎችን እና ነጻ ትምህርት ዕድል ልገሳ ፕሮግራሞችን ይመርምሩ።**
የዲሲ ነዋሪዎች በ OSSE፣ DC TAG በኩል ሁለት ልዩ የነጻ ትምህርት ዕድል ልገሳ ፕሮግራሞች አሏቸው bit.ly/DCPSDCTAG እና Mayoral Scholars osse.dc.gov/MayorsScholars። በተጨማሪ PSAT ፈተናን በመውሰድ በርካታ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ The United Negro College Fund www.uncf.org እና The Hispanic Scholarship Fund www.hsf.net በኩል ለሚተዳደሩ የነጻ ትምህርት ዕድሎች ከውድድር ውስጥ ይገባሉ።

## በልግ (ፎል)

☐ **ድርብ ምዝገባ**
የእኛ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአካባቢ ካሉ ኮሌጆች ወይም ዩኒቨርስቲ ክሬዲት የሚያዝላቸው ኮርሶችን መውሰድ ይችላሉ። በ GW Early College Program በ Schools Without Walls HS እና በ Banneker/McKinley HS Howard University Early College Program የተመዘገቡ ተማሪዎች ሁለቱንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የኮሌጅ ክሬዲት (ድርብ ክሬዲት) ለበተሳካ ሁኔታ የተፈቀዱ ኮርሶችን መውሰድ ነጥብ ሊያዝላቸው ይችላሉ። በተጨማሪ፣ ድርብ ክሬዲት በ UDC-CC ለሚገኙ 13 ኮርሶች ከትምህርት ቤት አማካሪ እና ርዕሰ መምህር ፈቃድ በማግኘት ብቁ ለሚሆኑ ተማሪዎች ሊሰጡ ይችላሉ። የድር ገጹን በ dcps.dc.gov/service/dual-enrollment-program ላይ ይጎብኙ ወይም የእርስዎን ትምህርት ቤት አማካሪ ስለ ድርብ ምዝገባ ዕድሎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ያነጋግሩ።

☐ **ለ OSSE Scholars Program ማመልከቻ ማስገባትን ከግምት ያስገቡ።**
3.2 ጂፒኤ ወይም ከዚያ በላይ ያላቸው በመማሪያ ክፍል ውስጥ እና ከመማሪያ ክፍል ውጪ የአመራር ክህሎቶችን በተግባር የሚያንጸባርቁ የዲሲ ከመጨረሻው አንድ ዓመት የቀራቸው ተማሪዎች የእነርሱን የኮሌጅ ተሞክሮ አስቀድመው ለመጀመር እንዲችሉ ለ OSSE Scholars ፕሮግራም ማመልከት አለባቸው። በዚህ ነጻ ፕሮግራም በኩል፣ ተማሪዎች በጥብቅ በመላው አገሪቱ በሚገኙ ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ዩኒቨርስቲዎች ለሚሰጡ የበጋ ኮርሶች ገብተው ለመማር ይችላሉ። ፕሮግራሙ በኮሌጅ ደረጃ ለሚሰጥ ትምህርት ቀደም ብሎ የመተዋወቅ ዕድልን ያጎናጽፋል እናም በአንዳንድ የተወሰኑ ዩኒቨርስቲዎች የኮሌጅ ክሬዲት ያስገኛል። ማመልከቻ ማስገቢያ ቀን በኦክቶበር 30 ያበቃል። (bit.ly/DCPSOSSEScholars)

☐ **ልጅዎ በኦክቶበር ለሚሰጠው የ PSAT ፈተና እንዲዘጋጅ ያግዙት።**
ይህ ተማሪዎች ለ SAT® እንዲለማመዱ እና የእነርሱን አካዳሚያዊ ክህሎቶች እንዲፈትሹ የሚያግዝ በቅድሚያ የሚሰጥ ፈተና ነው። በፈተናው ጥሩ ውጤት የሚያገኙ ተማሪዎች በተጨማሪ ለነጻ የትምህርት ዕድሎች ብቁ ይሆናሉ። ስለ PSAT bit.ly/DCPSPSAT ላይ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ። ልጅዎ ለ SAT እንዲዘጋጅ ለማገዝ Khan Academy/College Board Test Prep khanacademy.org/test-prep/sat፣ የሚለውን ይመርምሩ ይህ ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ያለ ምንም ክፍያ በነጻ ሊገኝ ይችላል።

CollegeBoard

ይህ ክፍል የተዘጋጀው በ DCPS እና በኮሌጅ ቦርድ መካከል ባለው የትብብር ስምምነት ነው።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# ክረምት

☐ **የ PSAT ውጤቶችን በጋራ ገምግሙ።**
የልጅዎ ውጤት ሪፖርት ከነጻ የ SAT ጥናት ዕቅድ ጋር አብሮ ይመጣል።
ይህ የመስመር ላይ (ኦንላይን) ብጁ የተደረገ ዕቅድ በእርስዎ ልጅ የፈተና ውጤቶች ላይ የተመረኮዘ ነው እናም እሱ ወይም እሷ ማሻሻል የሚገባቸው ትምህርት አካባቢዎችን እንዲሠራባቸው/እንድትሠራባቸው ሊያግዘው/ዛት ይችላል
bit.ly/DCPSPlanningKit።

☐ **ከመጨረሻው አንድ በቀረው ክፍል ላይ ያለውን ተማሪ ልጅዎን SAT Subject Tests™** እንዲወስድ ያበረታቱት። የእርስዎን ልጅ ክህሎቶች በተወሰኑ አካዳሚያዊ አካባቢዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመገመት በርካታ ኮሌጆች እነዚህን ፈተናዎች እንዲወሰዱ ይጠይቃሉ ወይም አጥበቀው ይመከራሉ። በአጠቃላይ አነጋገር፣ ተዛማጁን ኮርስ ከተማሩ በኋላ Subject Test ወዲያውኑ መውሰድ ተመራጭነት አለው። 3>ስለ SAT Subject Tests bit.ly/DCPSSATTest ላይ ተጨማሪ ይወቁ።

☐ **ልጅዎ ለ SAT እንዲዘጋጅ ያግዙት።**
ሁሉም የ DCPS ከመጨረሻው ዓመት አንድ የቀራቸው ተማሪዎች SAT በማርች ወር ውስጥ በነጻ በትምህርት ያለበት ቀን ይወስዳሉ። SAT ን ቀደም ብሎ መውሰድ የ DCPS ተማሪዎች ወደፊት እንዲቀጥሉ እና ለኮሌጅ ትምህርት ዕቅድ ማውጣት እንዲጀምሩ እና ነጻ የትምህርት ዕድሎችን ለማግኘት ማመልከቻ እንዲያስገቡ ያስችላቸዋል።

☐ **ልጅዎ የ AP Exams ፈተናዎችን እንዲወስድ ያበረታቱት።**
የእርስዎ የ 11ኛ ክፍል ተማሪ ልጅዎ Advanced Placement (AP) ወይም ሌላ የላቁ ትምህርቶችን የሚወስድ ከሆነ፣ እነዚህን ፈተናዎች በሜይ ወር ላይ ስለመውሰድ እሱ ወይም እሷ ከመምህራኑ/ኗ ጋር እንዲነጋገሩ ያድርጉዋቸው። ስለ AP Program በ DCPS bit.ly/DCPSAdvancedPlacement ተጨማሪ ያንብቡ።

☐ **የሚቀጥለውን ዓመት ትምህርቶች በተመለከተ ተወያዩ።**
የእርስዎ ልጅ ራሱን እንደሚፈትን እና የኮሌጅ ምዝገባ ፈቃድ ሰጪ ኃላፊዎች እንዲወስድ የሚጠብቁበትን ትምህርቶች መውሰዱን ያረጋግጡ። ኮሌጆች ስለሚፈልጉዋቸው ስለ AP እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርቶች apstudent.collegeboard.org/exploreap ላይ ተጨማሪ ይወቁ።

# ጸደይ (ስፕሪንግ)

☐ **የእርስዎን ልጅ ፍላጎት የሚያሟሉ ኮሌጆችን አብረው ከልጅዎ ጋር ይፈልጉ።**
ልጅዎ በኮሌጅ ትምህርት ማግኘት ስለሚፈልገው ጥራት እና ዓይነት አንዴ ሐሳቡን ካገኙ በኋላ ኮሌጆችን በ My College Fact Finder ይፈልጉ mcff.osse.dc.gov ለዲሲ የመመረቅ መቻል ዕድሎች በመቶኛ፣ የኮሌጅ ውጤቶች በመስመር ላይ (ኦንላይን) www.collegeresults.org በአገር አቀፍ ደረጃ የመመረቅ መቻል ዕድሎች በመቶኛ፣ በሚከተለው አድራሻ ላይ ላይ እንዲያመለከት ወይም እንድታመለከት ከግምት መግባት ያለባቸውን ኮሌጆች ዝርዝር እንዲፈጥር/እንድትፈጥር ያግዙት/ዟት:- በ Family Connections ትር በ Naviance ውስጥ bit.ly/DCPSFamilyConnection. ውስጥ እንዴት መድረስ እንደሚችል ተጨማሪ ይወቁ።

☐ **ልጅዎ ነጻ የትምህርት ዕድሎችን እንዲፈልግ ያግዙት።**
በጋ ፍላጎቶች ምን እንደሆኑ መርምሮ ለማወቅ እና አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር ትክክለኛው ጊዜ ነው እና ኮሌጆችም ትርጉም ያለው የበጋ እንቅስቃሴዎችን ያደረጉ ተማሪዎችን ይፈልጋሉ። የእርስዎ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ልጅዎ በዚህ በመጪው በጋ ፍላጎቱ የተነሳሳ እንዲሆን ማድረግ የሚችሉባቸውን አምስት መንገዶች bit.ly/DCPSSummer ያግኙ፤ የ DC Summer Youth Employment bit.ly/DCPSsyep ን ከግምት ያስገቡ። NAF Academy ተማሪዎች ከአካባቢ የኮሌጅ እና የሥራ መስክ አስተባባሪ ጋር ስለ በጋ NAF የትምህርት ላይ እያሉ ስለ NAF internships የሥራ ልምምድ በተመለከተ መነጋገር አለባቸው። ነጻ ድርብ የበጋ ምዝገባ UDC-CC dcps.dc.gov/node/1013692 ላይ እና በአካባቢ ባሉ ኮሌጆች ስላሉ ዕድሎች Family Connection ን በድረገጽ አድራሻ bit.ly/DCPSFamilyConnection ላይ ወይም College Greenlight for Nation Wide Opportunities bit.ly/DCPSSummerProgFinAid ላይ ያስሱ።

☐ **የኮሌጅ ባዛሮች እና የገንዘብ እርዳታ ዝግጅቶችን ይካፈሉ።**
እነዚህ ዝግጅቶች የኮሌጅ ወኪሎችን በአካል አግኝተው እንዲተዋወቁ እንዲሁም ለጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ያስችልዎታል። በእርስዎ አካባቢ እንዴት ዝግጅቶችን ማግኘት እንደሚቻል የእርስዎ ልጅ የትምህርት ቤቱን አማካሪ መጠየቅ ይችላል። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት College Fair Checklist የሚለውን bit.ly/DCPSChecklist ላይ ይፈትሹ።

☐ **ልጅዎ የበጋ ዕቅዶችን እንዲያወጣ ያግዙት።**
በጋ ፍላጎቶች ምን እንደሆኑ መርምሮ ለማወቅ እና አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር ትክክለኛው ጊዜ ነው እና ኮሌጆችም ትርጉም ያለው የበጋ እንቅስቃሴዎችን ያደረጉ ተማሪዎችን ይፈልጋሉ። የእርስዎ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ልጅዎ በዚህ በመጪው በጋ ፍላጎቱ የተነሳሳ እንዲሆን ማድረግ የሚችሉባቸውን አምስት መንገዶች bit.ly/DCPSSummer እና DC Summer Youth Employment ን ከግምት ያስገቡbit.ly/DCPSsyep ጭምር ከግምት ያስገቡ።

ለነጻ የኮሌጅ ዕቅድ አወጣጥ ሊጎች ግብዓቶች፣ የሚከተለውን ይጎብኙ:-

**bit.ly/DCPSCollegePrep11**

# የቤተሰብ ኮሌጅ ዕቅድ፡-
## 12ኛ ክፍል

ይህ ክፍል የተዘጋጀው በ DCPS እና በኮሌጅ ቦርድ መካከል ባለው የትብብር ስምምነት ነው።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

በ 2020፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከሚኖሩት ሥራ መስኮች 76 በመቶ የሚሆኑት ከሁለተኛ ደረጃ በተወሰነ መልኩ ከፍ ያለ ትምህርት መማርን የሚጠይቁ ይሆናሉ። ሁሉም ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በእነዚህ የሥራ ዘርፎች ብቁ እንዲሆኑ እና ለስኬታማነት እንዲዘጋጁ እንፈልጋለን። ይህ ግብዓት ወላጆች እና ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለማገዝ እንዲችሉ የእርስዎን ልጅ ወደ ኮሌጅ እና በኮሌጅ ውስጥ በስኬታማነት እንዲጓዝ ደጋፊ መረጃን ይሰጣል።

የመጨረሻው ዓመት በእንቅስቃሴዎች መዓት የተሞላ ነው። ይህ ልጅዎ የትምህርት ቤት ሥራን፣ ከሥርዓተ ትምህርት ተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎችን፣ እና የኮሌጅ ማመልከቻ ማስገባት ሂደትን የሚያመጣጥንበት ትልቅ ዓመት ነው። ይህን በጣም አስፈላጊ የሆነ ሂደት እርስዎ እና ልጅዎ በተሳካ ሁኔታ እንድታልፉት ከዚህ በታች የተሰጡትን ምክሮች ይጠቀሙባቸው።



## በጋ

- [ ] **ልጅዎ ማመልከቻ ማስገባት እንዲጀምር ያበረታቱት።**
  እሱ ወይም እሷ አሁን የሚፈለገውን ያክል መረጃ በኮሌጅ ማመልከቻዎች ላይ የተቻለውን/ላትን ያክል በመሙላት ቀላሉን ነገር አጠናቆ መቆየት ይችላል/ትችላለች። እንዴት ማመልከቻዎችን ማስገባት መጀመር እንደሚቻል bit.ly/DCPSHowToBegin ላይ ያንብቡ።

- [ ] **የዲሲ የነዋሪዎች የትምህርት ዕድሎችን እና ነጻ ትምህርት ዕድል ልገሳ ፕሮግራሞችን ይመርምሩ።**
  የዲሲ ነዋሪዎች በ OSSE፣ DC TAG እና Mayoral Scholars በኩል ሁለት ልዩ የነጻ ትምህርት ዕድል ልገሳ ፕሮግራሞች አላቸው። (dconeapp.dc.gov) የማመልከቻ መስፈርት እና ተገቢነት ያላቸው ኮሌጆችን ይገምግሙ። የእርስዎ ልጅ ተገቢነት ወዳለው ኮሌጅ ማመልከቻ እያስገባ ያለ መሆኑን ያረጋግጡ።

- [ ] **ልጅዎ በኦክቶበር ለሚሰጠው SAT ፈተና እንዲዘጋጅ ያግዙት።**
  ሁሉም የ DCPS የመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች SAT በኦክቶበር ወር ላይ በነጻ በእነርሱ ትምህርት ቤት ውስጥ በነጻ እንደገና ይፈተናሉ። በርካታ ኮሌጆች የተማሪዎችን ማመልከቻዎች ሲመዝኑ የተማሪዎችን የ SAT ውጤቶች አተኩረው ይመለከታሉ — ጥሩ ውጤት ማግኘት አስፈላጊ ነው። የእርስዎ የ 12ኛ ክፍል ተማሪን ለመግቢያ ፈተናዎች እና የምዝገባ መስፈርቶች እንዴት እንዲዘጋጅ ሊያግዙት እንደሚችሉ bit.ly/DCPSAdmissionPrep ላይ ተጨማሪ ይወቁ።

## በልግ (ፎል)

- [ ] **ከኦክቶበር 31 በፊት ከመጨረሻ ዓመት ተማሪ ልጅዎ አማካሪዎች ጋር ተገናኝተው ይነጋገሩ።**
  በዚህ ዓመት፣ ልጅዎ ከአማካሪው ጋር የኮሌጅ ማመልከቻዎችን ለመሙላት እና ለማስገባት አብሮ ይሠራል። የማመልከቻ ማስገቢያውን የጊዜ ሰሌዳ እና የሚጠበቁ የገንዘብ እርዳታዎችን የበለጠ ለመረዳት፣ ልጅዎን እንዴት በተሻለ መንገድ መርዳት እንደሚችሉ ለማወቅ ስለምርቃቱ ያለበት ሁኔታ ለመገምገም፣ እና የልጅዎን የመግባቢያ ሰነድ ደብዳቤ ለመፈረም ከእርስዎ የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ልጅዎ ከፍተኛ አማካሪ ጋር በዚህ በልግ ወራት (ፎል) ላይ የሚኖሩትን ሁሉንም ስብሰባዎች በአካል መገኘትዎ በጣም አስፈላጊ ነው። በሚከተለው አድራሻ ላይ ወደ ኮሌጅ ማመልከቻ ማስገባት ላይ የአማካሪውን ሚና በይበልጥ ይረዱ፡-
  bit.ly/DCPSApplyingtoCollege።

- [ ] **ከእርስዎ ልጅ ጋር የኮሌጅ ማመልከቻ ማስገቢያ ቀን መቁጠሪያ ይፍጠሩ።**
  ይህ የማመልከቻ ማብቂያ ቀኖችን እና ሌሎች አስፈላጊ ቀኖች ማካተት አለበት። የእርስዎ ልጅ በግልጽ የተቀመጡ የኮሌጅ ማመልከቻ ማስገቢያ ማብቂያ ቀናትን በ Family Connections በእርስዎ የሚከተለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድር ጣቢያ ላይ ማግኘት ይችላል፡-
  bit.ly/DCPSFamilyConnection። የእርስዎ ልጅ ኮሌጆችን ሲጨምር፣ የኮሌጅ ማመልከቻ ማስገቢያ ማብቂያ ቀናትን የሚያሳይ ብጁ የቀን መቁጠሪያ መስመር ላይ (ኦንላይን) ማግኘት ይችላል።

CollegeBoard

CollegeBoard

ይህ ክፍል የተዘጋጀው በ DCPS እና በኮሌጅ ቦርድ መካከል ባለው የትብብር ስምምነት ነው።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# በልግ ካለፈው የቀጠለ

☐ **የእርስዎን የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ማመልከቻዎች ለመከታተል ፍቃደኝነትዎን ይግለጹ።**
ሆኖም ግን ይህ የልጅዎ የሥራ ግዴታ እንደሆነ ያስታውሱ እና እንደ አማካሪ እና ፈደል አርታዒ በመሆን ያልዎትን ሚና ይገድቡ እንዲሁም የልጅዎን ውሳኔ ያክብሩ።

☐ **ልጅዎ ነጻ የትምህርት ዕድሎችን ፈልጎ እንዲያገኝ እና እንዲያመለክት ያግዙት።**
እሱ ወይም እሷ ስለ ነጻ የትምህርት ዕድሎች ከትምህርት ቤቱ አማካሪ ሊረዳት/ልትረዳ ይችላል/ትችላለች። የእርስዎ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የነጻ ትምህርት ማመልከቻዎን መጠየቅ እና መሙላት እንዲሁም በጊዜው ማስገባት አለበት። ስለ ነጻ የትምህርት ዕድሎች bit.ly/DCPSScholarshipFind።

☐ **የእርስዎ ልጅ የኮሌጅ ቃለ መጠይቆችን እንዲያዘጋጅ ያበረታቱት።**
ቃለ መጠይቅ ልጅዎ ስለኮሌጅ እና ኮሌጁም ስለ የእርስዎ ልጅ እንዲያውቁ የሚያስችል ምርጥ ዘዴ ነው። ስለ ቃለመጠይቅ አደራረግ ሂደቱ አጠቃላይ ዕይታ ከሚከተለው አድራሻ ላይ ያግኙ፦ bit.ly/DCPSCollegeInt።

# ክረምት

☐ **እርዳታ ለማግኘት ማመልከቻ ለማስገባት ከፌብሩዋሪ 28 በፊት FAFSA ይሙሉ።**
መንግሥት እና በርካታ ኮሌጆች እርዳታ ለመስጠት FAFSA ን ይጠቀማሉ። ይህን ማድረግ ከሙቸውም ጊዜ ይልቅ ቀላል ሆኗል ምክንያቱም በአውቶማቲክ የእርስዎን የግብር ከፋይነት መረጃ ከ IRS ወደ FAFSA መስመር ላይ (ኦንላይን) ማስተላለፍ ይችላሉ። እንዴት FAFSA መሙላት እንደሚችሉ እና የበለጠ ለማወቅ ይህን ያንብቡ፦ bit.ly/DCPSFinancialAid101።

☐ **የ DC TAG ማመልከቻ ከፌብሩዋሪ 28 በፊት ያስገቡ።**
አንድ ጊዜ የእርስዎን FAFSA ከሞሉ በኋላ፣ ወዲያውኑ የ DCTAG ማመልከቻ ወደ ለዲሲ ነዋሪዎች ብቻ የሚሰጡ ነጻ የትምህርት ዕድሎችን ለማግኘት ይሙሉት፦ https://dconeapp.dc.gov/። DC TAG እስከ $10,000 የሚደርስ ገንዘብ በስቴት ውስጥ እና ከስቴት ውጭ ላሉ የሕዝብ የአራት ዓመት ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች በመላው ዩኤስ አሜሪካ፣ ጓዋም እና ፖርቶ ሪኮ ልዩነቱን ለመክፈል እርዳታ ይሰጣል። DC TAG በተጨማሪ በአንድ አካዳሚያዊ ዓመት እስከ $2,500 የሚደርስ የትምህርት ክፍያ ለግል ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲች በዲስትሪክቱ እና በግል Historically Black Colleges and Universities (HBCUs) እና የሁለት ዓመት የኮሌጅ ትምህርት በአገር አቀፍ ደረጃ ወጪ ይሸፍናል።

# ክረምት ካለፈው የቀጠለ

☐ **አስቀድመው ግብርዎን ይክፈሉ።**
የእርስዎን ግብሮች በተቻለ ፍጥነት ፋይል ያስገቡ፣ ነገር ግን Free Application for Federal Student Aid (FAFSA) የእርስዎ ግብሮች የተሟሉ ስላልሆኑ ማመልከቻውን መሙላቱን አያዘግዩ። በ FAFSA ላይ የእርስዎን ገንዘብ ነክ መረጃ በግምት መስጠት እና በኋላ ላይ ማጠናቀቅ ይቻላል።

# ጸደይ (ስፕሪንግ)

☐ **ልጅዎ የኮሌጅ ምላሾችን እንዲያስተናግድ ያግዙት።**
አንድ ጊዜ የእርስዎ ልጅ ከኮሌጆች ስለ መግቢያን ማለፍ እና የገንዘብ እርዳታ በተመለከተ መረጃ ማግኘት እንደጀመረ ምን ማድረግ እንዳለበት ለመወሰን የእርስዎን እገዛ ይፈልጋል። ስለ ኮሌጅ እንዴት መምረጥ ይቻላል፦ bit.ly/DCPSNowWhat።

☐ **የገንዘብ እርዳታ ስጦታዎችን አንድ ላይ በመሆን ገምግሙ።**
የእርስዎ የ12ኛ ክፍል ተማሪ የገንዘብ እርዳታ ሽልማትን የሚገልጹ ደብዳቤዎችን ለማንበብ የትኛው ፓኬጅ የተሻለ እንደሚሆን ለማወቅ የእርስዎ እገዛ ያስፈልገዋል። የእርስዎ ልጅ የቅበላ ማናቸውንም ማብቂያ ቀኖችን በጥንቃቄ እየተመለከተ መሆኑን ያረጋግጡ። በገንዘብ እርዳታ ስጦታዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ ከሚከተለው ያግኙ፦ bit.ly/DCPSUnderstandingAwardLetter።

☐ **የኮሌጅ የቅበላ ማረጋገጫን የወረቀት ሥራዎች እንዲያጠናቅቅ የእርስዎን ልጅ ያግዙት።**
አንድ ጊዜ የእርስዎ ልጅ የትኛው ኮሌጅ ገብቶ መማር እንደሚፈልግ ከወሰነ በኋላ የኮሌጁን የቅበላ ግብዣ መቀበል፣ የትምህርት ክፍያ ተቀማጭ ገንዘብ መላክ፣ እና ሌሎች አስፈላጊ የወረቀት ሥራዎችን ማሟላት እና ማቅረብ ይኖርበታል። ስለ የእርስዎ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ቀጣይ እርምጃዎች ተጨማሪ ከዚህ ላይ ይረዱ፦ bit.ly/DCPSChoice።

ነጻ የኮሌጅ ዕቅድ አወጣጥ ግብዓቶችን ለማግኘት ይህን ይጎብኙ፦

**bit.ly/DCPSCollegePrep12**